# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

፩ኛ ሰንበት (እሑድ)፥ (ከመስከረም አንድ እስከ ሰባት ዕለታት እሑድ ቢውል)

በዚህ ቀን የሚዘመረው የቅዱስ ያሬድ መዝሙር፣ የሚቀደሰው ቅዳሴ፣ በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአጠቃላይ የሥርዓት ማኅሌቱ፣ ሥርዓተ ቅዳሴው፣ የሥርዓት አምልኮቱ ማዕከል የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ሕይወት ምስክርነት፣ አገልግሎት፣ ስለ ስመ እግዚአብሔር፣ ስለ ቃለ እግዚአብሔር መሞቱን መጥምቀ መለኮት በመሆኑ ያለውን ክብር የሚገልጽና የሚያስገነዝብ ነው።

## የዕለቱ ምስባክ

ሣህል ወርትዕ ተራከባ
ጽድቅ ወሰላም ተስዐማ
ርትዕሰ እምድር ሠረፀት

ምኅረትና እውነት ተገናኙ
ጽድቅና ሰላም ተሣሣሙ
እውነት ከምድር በቀለች

መዝ (፹፬፥፲-፲፩)

ይህ ምስባክ (ሳሕል ጽድቅ) ጌታ በተጠማቂነት (ርትዕ ሰላም) ዮሐንስ በአጥማቂነት በዮርዳኖስ መገኘታቸውን ዮሐንስ የራሱን ምድራዊነት የጌታን ሰማያዊነት እየሰበከ ከጌታ ጋር መገናኘቱን የሚያስተምር የመዝሙር ክፍል ነው። (አንድምታ ዳዊትን ይመልከቱ)

ወንጌል፥ ዮሐ ፩፥፲፭-፴፰
ቅዳሴ፥ የቅዱስ አትናቴዎስ

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ዮሐንስ አኅድዐ
«ዮሐንስ መሰከረ»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፲፩፥፲፯-ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕ ፪፥፩-፲፬ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፰፥፳፬-ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### የቅዱስ ዮሐንስ ምስክርነት

የእግዚአብሔር ሰው ቅዱስ ዮሐንስ በፈቃደ አምላክ በብሥራተ መልአክ ከካህኑ ከዘካርያስ መካን ከነበረችው ከኤልሳቤጥ ተወለደ ፅንሰቱ፣ ልደቱ በአጠቃላይ ስለ ልጅነቱ ሁኔታ እና እስተዳደጉ (ሉቃ ፩፥፭-፳፭) እንዲሁም ከቁ. ፶፯-፹ ይመልከቱ።

ዛሬ በቅዳሴ ሰዓት የተነበበልን ወንጌል ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንደጻፈው የዮሐንስን ምስክርነት ትምህርት የሚያስገነዝብ ነው። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ያለ አንዳች ማመንታት አሰምቶ ስለ ክርስቶስ መሰከረ ቀዳማዊነቱን ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ነበረ በማለት መሰከረ (ዮሐ ፩፥፲፭ ። ዮሐ ፩፥፮-፰) በክርስቶስ ስለተገኘው ጸጋም «… በጸጋ ላይ ተሰጠን … ጸጋና እውነት በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነልን» ብሎ መሰከረ (ዮሐ ፩፥፲፯)።

ከዚህ በተጨማሪ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እና ማንም ያላየውንና በባሕርዩ የማይመረመረውን አባቱን እንደሰበከልን መሰከረ (ዮሐ ፩፥፲፰)። አንተ ማን ነህ? ብለው ለሚጠይቁት ሰዎችም ክርስቶስ ወይም ኤልያስ አለመሆኑን ገልጸ ቃለ-ዓዋዲ መሆኑን አስረግጦ መረጃ ጠቅሶ ለሚጠይቁት ክፍሎች ከመመስከሩም በላይ ክርስቶስ መሆኑ ቀርቶ የክርስቶስን የእግሩን ጫማ ማሰሪያ ለመፍታትና ጫማውን ለመሸከም እንኳ ያልተገባ ሰው እንደሆነ በፍጹም ትህትና መሰከረ (ዮሐ ፪፥፲፱-፳፰) ክርስቶስም ወደ እርሱ ሲመጣ በማየቱ ተደንቆና በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ልቆ እርሱን ለሚከተሉት «… የዓለም ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ» በማለት መድኃኒትነቱን መሰከረልን (ዮሐ ፩፥፳፱)። ከዚህ በተጨማሪ ለሚጠይቁት ሁሉ በዮርዳኖስ ያየውን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ጌትነት መመስከሩንና በእውነት ላይ ያላመጸች ለእውነት የቆመች ሕይወቱን የተነበበልን የወንጌል ክፍል ያስገነዝበናል።

የዮሐንስ ሕይወት፥ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ከእናቱ ማኅፀን ሳለ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ፈጣሪውን ያወቀ (ሉቃ ፩፥፲፫-፲፯ / ፵፩)

- በምድረ በዳ በናዝራዊነት ለእግዚአብሔር ተለይቶ ያደገ (ሉቃ ፩፥፶፯-፹)
- ኃጢአተኞችን ስለ ኃጢአታቸው የወቀሰ

ከእግዚአብሔር የተላከ ቅዱስ ሰው ነበረ (ማቴ ፫፤፩-፲፪ ። ማር ፩፤፩-፰)።

- ተራራ የሆነውን ትዕቢተኛውን የሰው ልቦና በትምህርቱ የሚደንን፣ በተንኮል፣ በጠሊቅ ምክር የተራቀቀውን ልቡና በጽድቅ ቃል የሚመላ
- የተጣመመውን የሰው ልጆች የሕይወት መስመር በማስተካከል ሥጋ የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን እንዲያይ የሚያደርግ (ሉቃ ፫፤፩-፲፯ ። ዮሐ ፩፤፳፱)።
- ኢየሱስ ክርስቶስን ለማጥመቅ የበቃ በፈጣሪው አንደበት ከእሱ የሚበልጥ የለም ተብሎ የተነገረለት (ማቴ ፫፤፬ ። ማቴ ፲፩፤፲፩)።
- የብሉይ ኪዳን ማክተሚያ የሐዲስ ኪዳን መግቢያ የነቢያት መደምደሚያ (ሉቃ ፯፤፲፰-፴፭ ። ሉቃ ፲፮፤፲፮)።
- በኤልያስ መንፈስ ስለ ሕገ እግዚአብሔር በመቅናት ወንጌልን በመስበክ በኃጢአት፣ በከንቱ ነገር የሸመገለውን የሰዎችን ልቡና እንደ ሕፃናት ልቡና እስኪሆን ድረስ በወንጌል ቃል የሚለውጥ ባለማወቅ ሕፃን የሆነውን የሰው ልጆች ልቡና በእውቀት የሚያሸመግል (ሉቃ ፩፤፲፯ ። ማቴ ፲፯፤፱-፲፫) ሰው ነበር።

ቅዱስ ዮሐንስ ግብዝነትን፣ የኃጢአትን ኑሮ ያለአንዳች ፍርሃት የሚቃወም ንጉሥ ነው ላክብረው፣ ንግሥት ናት ልፍራት፣ ድሃ ነው ልናቀው ሳይል ሁሉን በእግዚአብሔር ቃል የሚመክርና የሚገስጽ የእውነት ሰው ነበረ። ሄሮድስንና ሄሮድያዳን በሚያደርጉትና በሚፈጽሙት የዝሙት ሥራ ምክንያት አጥብቆ ስለተቃወማቸው ሄሮድስ አስበ ደነሰ አስበ ዝሙት (የኃጢአት የዝሙት ዋጋ) አድርጎ አሳሰረው፣ በኋላም ወለተ ሄሮድያዳ የዘፈንዋ ሽልማት እንዲሆንላት ጠየቀች በመሆኑም የእግዚአብሔር ሰው ዮሐንስ ስለ ሕገ እግዚአብሔር እንደታሰረ በሰይፍ አንገቱን ተመታ (ማር ፮፤፲፬-፳፱)።

የዮሐንስ አንገት በሰይፍ ይመታ፣ ዮሐንስ ይታሰር፣ ይሙት እንጂ እርሱ ይሰብከው የነበረው ቃለ እግዚአብሔር ወንጌል ግን የማይታሰር፣ የማይቆረጥ የማይሞት በመሆኑ ዮሐንስ ከሞተ በኋላ እንኳ የዮሐንስን ትምህርት በማራመድና በመከተል የተገኙ ብዙ ሰዎች እንደነበሩ ዛሬ በንፍቁ ቄስ የተነበበልን የሐዋርያት ሥራ ፲፰፤፳፬-፳፰) ያለው ቃል ይመሰክራል።

ዛሬም እኛ እንደ ዮሐንስ የእውነት ሰውን ስለ ልብሱ ስለ ሀብቱ ስለ ስልጣኑ ሳይሆን ስለ ማንነቱ የምናከብር ክፉዎችን በክፋታቸው የማንታገስ (ራዕ ፱፤፱-፫) የግብዝነት ሕይወት የሌለን ሰዎች እንድንሆን በሁለቱ ቀዳስያን ዲያቆናት የተነበቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያስገነዝቡናል (ያዕ ፱፤፩-፲፬ ። ፩ኛ ቆሮ ፲፩፤ ፲፮-ፍጻሜ)።

እንደ ቅዱስ ዮሐንስ ስለ ወንጌል የሚሞት የሚታሰር የሚንገላታ ሰው ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን ያስፈልጋታል። ዛሬም የእግዚአብሔር አገልጋዮች የዮሐንስን አሠረ-ፍኖት (ፈለግ) በመከተል በሥጋቸው የሚደክሙትን በመንፈሳቸው የሚዝሉትን እንድንመክርና እንድንገስጽ የተቀደሰው የቅዳሴ ክፍል ያስገነዝባል።

ጥቅስ፥ «ካህናት ሆይ ... ከወገናችሁ ውስጥ በፈሊጥ መርምሩ በመጸለይ ከእናንተ ጋር እንዳይቆምና እንዳይተባበር ሴሰኛም ቢሆን፣ ሌባም ቢሆን፣ ሐሰተኛም ቢሆን፣ እሊህም በአፍአ የሚፈረድባቸው አምስቱ ውሾች ናቸው።

ኃጢአታቸውን እንደወንድማችሁ ገስፁት ለሞት የሚያበቃ በደል ቢኖርበት በግልጽ ዝለፋት የበደለውን ምከሩት ያቺን መንገድ ይተው ዘንድ ይቅር ሊልለት ወደ እግዚአብሔር ይመለስ ዘንድ» (ቅዳሴ አትናቴዎስ ቁ. ፰ - ፲)።

ዛሬም እንደ ዮሐንስ ለእግዚአብሔር ጽድቅ ብንቆም ከዓመጸኞች ጋር ቁመን በሥራቸው እንዳንተባበር የምንቀድሰውና የምንሰማው ቅዳሴ ይመክረናል፤ ያስተምረናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።